## ስለኢትዮጵያ ፡ ቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ ጥያቄዎች ።

## ከጆርጅ ቹቹኖቪች ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔትን ፡ የሚያነቡ ፡ ከሚቀጥሉት ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ከታተሙት ፡ ከፀሐፊው ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ ጥያቄዎች ፡ ለተመረጡት ፡ ጥያቄዎች ፡ የተሻፈ ፡ መልስ ፡ ለመጽሔቱ ፡ በመስጠት ፡ የሕግ ፡ ዕውቀታቸውንና ፡ ለሕጋዊ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ የመስጠት ፡ ችሎታቸውን ፡ እንዲገምቱ ፡ (እንዲፈትኑ) ፡ ተጋብዘዋል ። በአማርኛም ፡ ሆነ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ተጽፎ ፡ ለመጽሔቱ ፡ የተሰጠ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ጥያቄ ፡ ብልጫ ፡ ያሳየው ፡ መልስ ፡ በታህሣሥ ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይወጣል ፡ ተብሎ ፡ በሚገመተው ፡ የመጽሔቱ ፡ ዘጠነኛ ፡ እትም ፡ ላይ ፡ ይወጣል ። መልሶቹ ፡ ከመስከረም ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ፡ም ፡ በፊት ፡ መሰጠት ፡ አለባቸው ። እያንዳንዱ ፡ መልሱ ፡ ለእትም ፡ የተመረጠለት ፡ ተካፋይ ፡ አንድ ፡ መልሱ ፡ የሚወጣበትን ፡ መጽሔትና ፡ አምበት ፡ የመልሱ ፡ ሌላ ፡ እትሞች ፡ በነፃ ፡ ይወስዳል ። ለአራቱም ፡ ጥያቄዎች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አጥጋቢ ፡ መልሶችን ፡ ለሚሰጥ ፡ ተካፋይ ፡ የዓመቱን ፡ መጽሔት ፡ እትም ፤ subscribtion ፡ አንድ ፡ መልሶችን ፡ የሚወጣበትን ፡ መጽሔትና ፡ የማንኛውንም ፡ የታተመ ፡ መልስ ፡ የፀሐፊውን ፡ ሌላ ፡ እትሞች ፡ በነፃ ፡ ያገኛል ፡ (ይወስዳል) ። ተካፋዮች ፡ ሁሉንም ፡ ጥያቄዎች ፡ እንዲመልሱ ፡ አይገደዱም ።

### <u>አንደኛ ፡ ጥያቄ ፤</u>

የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ የጻፈው ፡ ባለሞያ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬኔ ፡ ዴቪድ ፡[1] እንዳሳየው ፤ በጋብቻ ፡ የሚገኘው ፡ ዝምድና ፡ ጋብቻው ፡ ሲፈርስ ፡ ያልቃል ፡ (ይጠፋል) ፡ የሚለውን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ (ንድፍ) ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻው ፡ ቢፈርስም ፡ ዝምድናው ፡ ይኖራል ፡ እንዲል ፡ ፓርላማው ፡ ቀይሮታል ፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፩ን ፡ ተመልከት ።[2]

የፓርላማው ፡ ቅየራ ፡ በነዚሀ ፡ መስመሮች ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ውጤቶችን ፡ አስከትሏል ።

፩) ቀለብ ፡ የመሰጠት ፡ ግዴታወች ።

፪) ቀለብ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታዎች ።

---

- የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋከልቲ ።

1. አር ፡ ዴቪድ ፤ <u>ለ ፡ ድሯ ፡ ዴ ፡ ላ ፡ ፋሚል ፡ ዳን ፡ ለኮድ ፡ ሲቪል ፡ ኢትዮጵን ፡</u> (ሚላን ፤ ጉፍሬ ፡ እ.አ.አ. ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፶፩ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፩ ፡ ይመለከቷል ።
2. ቁጥር ፩፻፶፩ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—

   ቁ. ፩፻፶፩ ። <u>የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ መጨረሻ ።</u>

   ዝምድናውን ፡ ያስገኘው ፡ ጋብቻ ፡ ቢፈርስም ፡ በጋብቻ ፡ የተገኘው ፡ የቀጥታ ፡ ዝምድናና ፡ የጐን ፡ ዝምድና መተሳሰር ፡ እንደጸና ፡ ይኖራል ። (እዚህ ፡ ላይ ፡ መገንዘብ ፡ ያለብን ፡ የዚህ ፡ ቁጥር ፡ የድሮ ፡ አርእስት ፡ ከቁጥሩ ፡ ጽሑፍ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ የሚቃረን ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በግዴለሽነት ፡ ሳይታረም ፡ መቅረቱን ፡ ነው ።

## ሁለተኛ ፡ ጥያቄ ፤

በጸሐፊው ፡ ኮሚቴ ፡ (codification commission) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጨመረው ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፺፱ ፡ ቀድሞ ፡ ፯፻፲፫ ፡ ተደራራቢ ፡ ያደርገዋል ።[3]

፩) ይህ ፡ ተደራራቢ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ አባባል ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ልክ ፡ አይደለም ? ለምን ?

፪) የቁባት ፡ ውርስ ፡ የሕግ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ። በማለት ፡ በሕግ ፡ የፈረሰ ፡ ቢሆንና ፡ (አንቀጽ ፡ ፰፻፷፯)[4] ፡ የተጣሰው ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፲፫ ፡ ቢባል ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውሳኔ ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ወይንስ ፡ ልክ ፡ አይደለም ? ለምን ?

## ፫ኛ ፡ ጥያቄ ፤

የፀሐፊው ፡ ኮሚቴ ፡ (codification commission) ፕሮፌሰር ፡ ሬኔ ፡ ዴቪ ፡ በአቀረቧቸው ፡ ረቂቅ ፡ አንቀጾች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጥገናዎችንና ፡ ጭመራዎችን ፡ አድርጓል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በኮሚቴው ፡ የተጨመረውን ፡ አንቀጽ ፡ ፲፻፷፯፡ ይኸውም ፡ «ጋብቻው ፡ ለሚያስከትለው ፡ ውጤት የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በእውነት ፡ መፈጸሙ ፡ ወይም ፡ በግምት ፡ ተፈጽሟል ፡ መባሉ ፡ አይደለም» ፡ የሚለው ፡ ከሚከተሉት ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንዳጣጣሙ ፡ (አብረው ፡ እንዲሄዱ) ፡ ማድረግ ፡ እንችላለን?[5]

፩) በኮሚቴው ፡ የተጨመረው ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፺፩ ፡[6] (ሐ) እንደሚሰጠው ፡ ስለሚያገቡት ፡ ሰው ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት[7] ፡ ማድረግ ፡ አለመቻል ፡ የሚደረገው

---

3. የእነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ ጽሑፎች ፡ እንደሚከተሉት ፡ ናቸው ፦

ቁ. ፮፻፺፱ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ እንዲኖር ፡ ስላለመደረጉ ።

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ በሚኖሩት ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ መካከል ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ እንዲኖራቸው ፡ አያስቆጥራቸውም ።

ቁ. ፯፻፲፫ ፡ ለመንግሥት ፡ ስለ ማስተላለፍ ።

ዘመዶች ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሟቹ ፡ ሀብት ፡ ወራሽነቱ ፡ ለመንግሥት ፡ ይተላለፋል ።

4. በቁጥር ፰፻፷፯ ፡ ንኡስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፦

(፩) አንድ ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ለሕግ ፡ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

5. ከዚሁ ፡ በላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዴቪድ ፡ ገጽ ፡ ፶፰ ፡ ማስታወሻ ፡ ፵ ፡ ይመለከቷል በቁጥር ፡ ፲፻፷፯ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚለው ፦

ቁ. ፲፻፷፯ ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋው ፡ ግንኙነት ፡ መፈጸም ።

ጋብቻው ፡ ለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋው ፡ ግንኙነት ፡ በውነት ፡ መፈጸሙ ፡ ወይም ፡ በግምት ፡ ተፈጽሟል ፡ መባሉ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

6. እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፺፩ ፡ የአግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፳፪ ፡ የቁጥር ፡ ፰፻፺፩ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ቁ. ፰፻፺፩ ፡ (፪) የተወሰኑ ፡ ምክንያቶች ።

ማንኛውም ፡ መሳሳት ፡ የማይሆን ፡ ሆኖ ፤ ዋና ፡ መሳሳት ፡ የሚባሉት ፦ ....

(ሐ) በሚያገቡት ፡ ሰው ፡ ጤና ፡ ወይም ፡ ሰውነት ፡ መሳሳት ፤ ይኸውም ፡ ያገቡት ፡ ሰው ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ የያዘው ፡ ወይም ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

7. በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈውን ፡ ይመለከቷል ።

ስህተት ፡ ዋና ፡ ስህተት ፡ ነው ፡ (በአንቀጽ ፡ ፭፻፺፩ ፡ መሠረት ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል)[8] ።

፪) በኮሚቴው ፡ የረቀቀው ፡ (የተጻፈው) አንቀጽ ፡ ፭፻፺፪ ፡ (፫)[9] ፡ ስለሚለው ፡ የሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ የሚመሠረተው ፡ ከሌሎች ፡ ምክንያቶች ፡ ሌላ ፡ በሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መፈጸም ፡ ነው ።

<u>አራተኛ ፡ ጥያቄ ፡</u>

በፕሮፌሰር ፡ ዴቪድ[10] ፡ እንደተገለጠው ፡ ለፀሐፊው ፡ ኮሚቴ ፡ (codification commission) የቀረበው ፡ የረቂቅ ፡ አንቀጽ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የመኖርን ፡ መብት ፡ ሰጠው ፡ ኮሚቴው ፡ ይህን ፡ አንቀጽ አልተቀበለውም ፡ ምንም ፡ ምክንያቶች ፡ አልተጻፉም ፡ አለመቀበሉ ፡ ከነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አንዱን ፡ ማለት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

፩) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፳፰ ፡ ከአንቀጽ ፡ ፫ሺ፫፻፵፯(፩)[11] ጋር ፡ ተጣምሮና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፲፮ ፡[12] በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ቢከ

8. የቁጥር ፡ ፭፻፺፩ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚለው ፡—
ቁ. ፭፻፺፩ ። ስሕተት ።
(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ከዋና ፡ ስሕተት ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስለት ፡ ዳኞቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።
(፪) ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚሆነው ፡ ጥያቄ ፡ ስሕተቱን ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚቀጥለው ፡ (በድስት) ፡ ፮ ወር ፡ ውስጥና ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻው ፡ ከተፈጸመበት ፡ በሚከተሉት ፡ ፪ ፡ (ሁለት) ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ካልቀረበ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

9. ከዚህ ፡ በላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዴቪድ ፡ ገጽ ፡ ፺፪ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፳፱ ፡ መጨረሻ ፡ ያለውን ፡ ይመለከቷል ። የቁጥር ፡ ፭፻፺፪ ፡ ንኡስ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡
(፫) በተለይም ፡ ዳኞቹ ፡ የሚመለከቱት ፡ የተጋቢዎቹን ፡ በቅን ፡ ወይም ፡ በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ መሆን ፤ ሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ መፈጸሙን ፡ ወይም ፡ አለመፈጸሙን ፡ ያሉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከፈረሰው ፡ ጋብቻ ፡ የተወለዱትን ፡ ልጆች ፡ ጥቅምና ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሆኑትን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ጥቅም ፡ ነው ።

10. ከዚህ ፡ በላይ ፡ በእግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፭ ፡ የተመለከተውን ፡ ዴቪድ ፡ ገጽ ፡ ፺፯ ፡ የእግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፴፯ ፡ ይመለከቷል ።

11. የእነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጽሑፎች ፡ እንደሚከተሉት ፡ ናቸው ፡—
ቁ. ፰፻፳፰ ። <u>በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ</u> ።
አንድ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰረ ፡ ከሆነ ፡ ጋብቻው ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ሁለተኛ ፡ ጋብቻ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።
ቁ. ፫ሺ፫፻፵፯ ። የተሻሩ <u>፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች</u> ።
(፩) ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፤ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ስለተተካ ፡ ተሽረዋል ።

12. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፲፮ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ቁ. ፮፻፲፮ ። <u>በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ስለማድረግ</u> ።
(፩) ሕግ ፡ የሚያጸናው ፡ ዐይነት ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ግዴታ ፡ ታስሮ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ የፊተኛው ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ሳይፈርስ ፡ ወይም ፡ ሳይሻር ፡ ከሌላ ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ብሎ ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፤
በእስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ በተለይም ፡ አድራጊው ፡ እውነተኛውን ፡ ሁኔታ ፡ በመሰወር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አዲሱን ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ የምትፈጽመውን ፡ ሴት ፡ በማታለል ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል።
(፪) ሚስት ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ ግዴታ ፡ ታስራ ፡ የምትገኝ ፡ ሴት ፡ መሆንዋን ፡ ከዚያች ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዐት ፡ የፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእስራት ፡ ይቀጣል ።
(፫) ከሁለቱ ፡ ጋብቻ ፡ አንዱ ፡ እስከፈረሰ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ተሻሩ ፡ ድረስ ፡ የወንጀሉ ፡ ክር ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ አይቆጠርም ።

ለክሉም ፡ ቅሉ ፡ የ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የቃዲያስና ፡ የናቢያስ ፡ ደርጐች ፡ ላይ ፤[13] የወጣው፡ ድንጋጌ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ የሚፈጽሙትን ፡ ተጋቢውች ፡ ጋብቻ ፡ (እስላሞች) ሕጋዊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርገዋል ።

፪) በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻዎች ፡ እንኳን ፡ ሕጋዊ ፡ ጋብቻዎች ፡ ሊሆን ፡ ይቅርና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የሚሰጠውን ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤቶችን፡ እንዳይሰጡ ፡ መከልከል ፡ አለባቸው ፡ (እነሱም ፡ በአንቀጽ ፡ ፯፻፲፩ ፤ ፯፻፲፭ ፤ ፯፻፲፯ ፡ የተጠቀሱት ፡ ናቸው ።)[14]

፫) ሳይቀበሉት ፡ የቀረው ፡ አንቀጽ ፡ የተጋነነ ፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ ለእንደዚህ፡ ዓይነት ፡ ውጤቶች ፡ ብዙዎቹ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻዎች ፡ በአንቀጽ ፡ ፯፻፰—፯፻፱ (፩) ለጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነትን ፡ ለመኖር ፡ የተሰጠው ትርጓሜ ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ ያሟላሉ ።[15]

፬) ጋብቻው ፡ በመጨረሻ ፡ ጽኑ ፡ እንዲሆን ፡ ከሚያስችሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ በቀር፡ (አንቀጽ ፡ ፯፻፲፫) ፤[16] በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ፍቺ ፡ እስካስከተለ ፡ ድረስ፡

13. የቃዲዎችና ፡ የናኤባዎች ፡ ጉባኤ ፡ ቤት ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፷፪ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፵፬) ፡ ዓ. ም. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ።

14. በእነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ጽሑፎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤—

ቁ. ፯፻፲፩ ። ሴትዮዋ ፡ ለምትገባባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ወንድየው ፡ ዋስ ፡ ስለመሆን ።

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ሁኔታ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ።

ለእርሱ ፡ ወይም ፡ ለርሱዋ ፡ ወይም ፡ ከግንኙነቱ ፡ ለተወለዱ ፡ ልጆች ፡ መኖሪያ ፡ ስትል ፡ ሴቲቱ ፡ ለፈረመቻቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ በአንድነት ፡ ኃላፊ ፡ ነው ።

ቁ. ፯፻፲፭ ። የልጆች ፡ መወለድ ።

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ መወለዳቸው ፡ የሚረጋገጠው ፡ ስለመወለድ ፡ በተባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቁ. ፯፻፲፯ ። (፪) እንዲያልቅ ፡ የሚያደርገው ፡ ወንድየው ፡ ሲሆን ።

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ግንኙነቱን ፡ እንዲያልቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ርትዕ ፡ ሲያስገድድ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ለሴትዮዋ ፡ ኑሮ ፡ የሚበቃ ፡ ኪሣራ ፡ ዳኞች ፡ እንዲከፍላት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላሉ ።

15. የእነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጽሑፋቸው ፡ እንደሚከተሉ ፡ ናቸው ፤—

ቁ. ፯፻፰ ። ትርጓሜ ።

ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በሕግ ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ጋብቻ ፡ ሳያደርጉ ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ በመኖር ፡ አድርገውት ፡ የሚገኘው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ቁ. ፯፻፱ ። ማጠናቀቂያ ።

(፩) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ሰውዬውና ፡ ሴትዮዋ ፡ የሚያሳዩት ፡ ሁኔታ ፡ በደንብ ፡ እንደተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ዐይነት ፡ መሆኑ ፡ አስፈላጊና ፡ በቂ ፡ ነው ።

16. የቁጥር ፡ ፯፻፲፫ ። ጽሑፉ ፡ የሚለው ፡

ቁ. ፯፻፲፫ ፡ (፫) ስለ ፡ ማጽናት ።

የመጀመሪያዩቱ ፡ ሚስት ፡ ለመኖሯ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ያለበት ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ተደርጓል ፡ የሚለው ፡ ነው ።

ለሁልጊዜ ፡ ጽኑ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆይ ፡ (አንቀጽ ፡ ፭፻፲፱ ፡ ከ፭፻፶፮ ፡ (፩—፪) ጋር) ፤ የተሰረዘው ፡ አንቀጽ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።[17]

እላይ ፡ ከተሰጡት ፡ ሐሳቦች ፡ አንዱን ፡ ምረጡና ፡ ተከራከሩ ፡ በሁለተኛውና ፡ በሦስተኛው ፡ ሐሳቦች ፡ ላይ ፡ ኮሚቴው ፡ ባልና ፡ ሚስቶች ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ለመኖር ፡ መፈቃቀድ ፡ ይችላሉ ፡ የሚለውን ፡ አንቀጽ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቶ ፡ አስገዳጅ ፡ በሆነው ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፵፫ ፡ (፪)[18] መተካቱን ፡ አስታውሱ ። (ልብ ፡ አድርጉ) ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነቶች ፡ በሕግ ፡ የታወቁና ፡ የሚመሩ ፡ መሆናቸውንም ፡ አስታውሱ ፡ (አንቀጽ ፡ ፭፻፳—፭፻፳፰ ፡)[19] ።

17. የእነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ ጽሑፎች ፡ እንደሚከተሉት ፡ ናቸው ፡—

ቁ. ፭፻፲፱ ፡ (፪) ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቁጥር ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ (ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት) ፡ እንደኛው ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ ይፈርሳል ። (ቁ. ፭፻፲፩) ።

(፪) ዳኞች ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚያደርጉት ፡ በማይጠራጠር ፡ አኳኋን ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ ባለቤት ፡ ጋብቻው ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በሕይወቱ ፡ መኖሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

ቁ ፡ ፭፻፶፮ ፡ መሪ ፡ ደንቦች ።

(፩) የጋብቻ ፡ ሁኔታዎች ፡ ከማጓደል ፡ የተነሣ ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ ዳኞች ፡ በሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ መፍረሱ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ በርትዕ ፡ ይወስናሉ ።

(፪) ፍቺ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙነት ፡ ለማጣራት ፡ በተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ዳኞቹ ፡ ይመራሉ ። (ከቁ ፡ ፭፻፺ ፡ እስከ ፡ ፭፻፶፩) ።

18. ከዚህ ፡ በላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዴቪድ ፡ ገጽ ፡ ፶፰ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፵፪ ፡ ይመለከቷል ።

ቁጥር ፡ ፭፻፵፫ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—

(፪) እንዲሁም ፡ ባል ፡ ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

19. እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በመጽሐፍ ፡ ሁለት ፡ (፪) ፡ በአንቀጽ ፡ አራት ፡ (፬) ፡ በስምንተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ (ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለመኖር) ፡ ያሉትን ፡ ያጠቃልላሉ ።